**አንቀጽ 1፡ <u>መቋቋም</u>**

የኢትዩጵያ ብሄራዊ ሰርከስ የተባለ ጥምረት በመስከረም 19 ቀን 2013 ዓ.ም ተቋቁሟል፡፡

**አንቀጽ 2፡ <u>ስያሜ</u>**

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ጥምረት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሰርከስ በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሰርከስ ጥምረት ተብሎ ይጠራል፡፡

**አንቀጽ 3፡ <u>የመስራቾች አባላት ዝርዝር</u>**

| ተ.ቁ | የሰርከሱ ሙሉ ስም | በስራቸው የሚገኙ የአባላት መጠን | አድራሻ ወረዳ ክ/ከተማ የቤት ቁጥር | ዜግነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአዲስ አበባ ሰርከስ ማህበር | 12 | አዲስ አበባ | |
| 2 | የአማራ ክልል ሰርከስ ማህበር | 13 | ባህርዳር | |
| 3 | የትግራይ ክልል ሰርከስ ጥምረት | 9 | መቀሌ | |
| 4 | የደቡብ ኢትዮጵያ ሰርከስ ማህበር | 7 | አዋሳ | |
| 5 | ድሬደዋ ሰርከስ | 1 | ድሬደዋ | |
| 6 | የኦሮሞያ ክልል ሰርከስ ማህበር | 2 | አዳማ | |
| 7 | ሰርከስ ቤኒሻንጉል | 1 | አሶሳ | |
| 8 | | | | |
| 9 | | | | |
| 10 | | | | |
| 11 | | | | |
| 12 | | | | |

**<u>አንቀጽ 4፡ ራዕይ (vision)፤</u>**

በ2022 ዓ.ም አንድ ብሄራዊ የሰርከስ ማሳያ ማእከል በመገንባት፣ የባለሙያ ደረጃ እርከን እንዲኖረው በማድረግ ብሄራዊና አለማቀፋዊ የሰርከስ ፌስቲቫሎችን በማዘጋጀት፣ ሰርከስን ፣ባህሉ ያደረገ ጤናማ አመለካከትና ክህሎት ያለዉ ሁለተናዊ

ስብዕናዉ የተሟላ በዓለም አቀፍ ደረጃ ምስጉን፣ተወዳዳሪና ዉጤታማ የሆኑ የሰርከስ አርቲስቶችን ቁጥር በማሳደግ በአፍሪካ ቀዳሚ የሰርከስ ተቋም ሆኖ ማየት፤

<u>አንቀጽ 5 ተልኮ (mission)</u> ፤

በሀገራችን የሰርከሶችን አንድነት በመፍጠር የሰርከስ ጥበብን በኢትዮጵያ እንዲስፋፋና እንዲያድግ በማድረግ ጥበቡ የሀገራችን የባህል ኢንዱስትሪ ምሰሶ እንዲሆን ማስቻል

<u>መርሆ</u>

ሁሉም የሰርከስ ዐይነቶች በተለያየ መልኩ የሚመጣ (የሚፈጠር) ዘርፍ ሆኖ ተጓዥ ወይም ቋሚ ትልቅም ይሁን ትንሽ የተለያዩ የሰርከስ ጥበቦችን፣የአክሮባት ትርኢቶችን፣ አስቂኝ ቀልደኞችን (ክላወኖችን) ፣ አስማተኞችን (ምትታዊ ትዕይንቶችን ሰሪ) ወ.ዘ.ተ በማካተት ከትንንሽ ህፃናት እስከ ትላልቅ አረጋውያን የዕድሜ ገደብ ሳይኖረው የህዝባችንን የዕለት ተዕለት ኑሮ ማሳያ ዘርፍ በማድረግ ባህልን አስጠብቆ በማስቀጠል እና ማህበራዊ ግንኙነትን በማጠናከር በማሰልጠን፣ በማስተማርና በማዝናናት ሁሉንም አይነት የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽና ተጠቃሚ ማድረግ፡፡

<u>ሰርከስ ለሁሉም!</u>

አንቀጽ 6 ፡ <u>ዓላማ</u>

<u>የማህበሩ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡</u>

ሀ. በአገራችን የሰርከስ ጥበብን በማስፋፋት፣ በማደራጀት፣ በማሰደግና በመከታተል ሁሉንም ክልሎች መደገፍ

ለ. በአገራችን እንዲሁም በክልሎች የሰርከስ ማዕከላትን በመገንባት እንዲስፋፋም ከአጋር አካላት ጋር በትብብ መስራት

ሐ. የሰርከስ ስልጠና ካሪክለም/ማንዋሎችን በማዘጋጀት ሳይንሳዊና ዘመናዊ በሆነ መልኩ በአገራችን የሰርከስ ስልጠና እዲሰጥ ማድረግ

መ. ሰርከስ በአገራችን የሚለካና የሚመዘን የኪነ-ጥበብ ዘርፍ እንዲሆን ከመንግስትና ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመስራት ዘርፉ ስታንዳርድ እንዲኖረው ማድረግ

ሠ.ከመላው አለም የሚገኙ መሰል ተቋማት እውቀቶችን በመቅሰምና የልምድ ልውውጦች ማድረግ የተገኙ ልምዶችንም በአገራችን ተግባራዊ ማድረግ

ረ. ለዘርፉ መንግስት አስፈላጊውን ትኩረትና ድጋፍ እንዲሰጠውና በፖሊሲ እንዲደገፍ ከመንግስትና ከባለድርሻ አካት ጋር በትብብር መስራት

ሰ. የአገራችን የባህል አምባሳደር በመሆን የሀገራችንን ታሪክና መልካም ገፅታ በመላው አለም ማስተዋወቅ

ሸ. በአገራችን ያሉ የሰርከስ ጥበብ ባለሞያዎች ሁሉ አቀፍ መብት እንዲከበር መታገል

ቀ. በሰርከስ ጥበብ የአገራችን ማህበረሰብ ማህበራዊ ችግሮቹን ማሳያ የኪነ-ጥበብ ዘርፍ እንዲሆን ከአገር በቀልና አለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች ጋር በመስራት በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ ማድረግ

በ. በአገራችን የሚከናወኑ አገራዊ ልማቶች ላይ ዘርፉ የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ማድረግ

ተ. አገራችን በሰርከስ ጥበብ የአፍሪካ መዲና (ማዕከል) ማድረግ

ቸ. ብሔራዊ፣አህጉራዊና አለምአቀፋዊ የሰርከስ ፌስቲቫሎችን በማዘጋጀት የሰርከስ ጥበብን በመላው ኢትዮጵያ ማስፋፋትና ተመራጭ የመዝናኛ ዘርፍ ማድረግ

ኀ. አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ሰዓት የሀገራችንን ልማት በመደገፍ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ አዝናኝ በሆነ መልኩ ትምህርታዊ እውቀትና ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡

ነ. በእህት የማህበሩ አባላትና በሃገር አቀፍ ደረጃ በሚኖረው የአርቲስቶችና ተማሪዎች ዝውውር ላይ በውልና በህግ የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ

ኘ. በሰርከስ ስም የሚከናወኑ ማንኛውም ዓይነት ህገወጥ ተግባራትን መከታተልና መገምገም ለህግ ተጠያቂ ማድረግ

ኘ. ጥምረቱን የአለም አቀፍ የሰርከሶች ጥምረት/ኔቶርክ ላይ አባል እንዲሆን ማድረግ

አንቀጽ 7፡ <u>የበጀት አመት</u>

የማህበሩ የበጀት ዓመት እ.ኢ.አ. ከሃምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል፡፡

አንቀጽ 8፡ <u>ትርጉም</u>

1. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሰርከስ ጥምረት ማለት ፡-ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበር ሲሆን የክልል ሰርከስ ማህበራትን በመስራችነት በመያዝ ፣የሰርከስ ድርጅት ባለቤቶችን፣ዳይሬክተሮችን፣ የፌስቲቫል አዘጋጆችን፣ አርቲስቶችንና ተመሳሳይ አላማና ፍላጎት ያላቸውን ድርጅቶችና ግለሰቦችን በተባባሪነትና በክብር አባልነት ያካተተ ጥምረት ነው፡፡
2. የበዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተገለጸው ቃላት ለሁለቱም ጾታዎች ተፈጻሚነት አለው፡፡
3. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡
4. "ጥምረት/ኔትዎርክ" ማለት የጋራ አላማ ያላቸው ማህበራት ለጋራ አላማቸው የሚመሰርቱት አደረጃጀት ነው
5. "ሰርከስ" ማለት የተለያዩ የሰርከስ ጥበቦች፣የአክሮባቲክ ችሎታዎችን፣የአስቂኝ (የክልውን) ስራዎችና የባህል መገለጫዎችን አካቶ የሚያቀርብ የትርኢት/ጥበብ አይነት ነው፡፡
6. "መስራች አባላት» ማለት ማህበሩ ያቋቋሙ እና በስራቸው አባላትን ይዘው የሚገኙ የቡድን መሪዎች ናቸው፡፡
7. «አባላት» ማለት የማህበሩ መስራች አባላቶች እና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የአባላትን መመዘኛ የሚያሟሉትን የቡድን መሪዎች ያጠቃልላል፡፡
8. «ንዑስ አባላት» ማለት በቡድኖች ስር ያሉ የቡድን አባላቶችን ይይዛል፡፡
9. «አካታች» ማለት ሁሉንመም ዓይነት የህብረተሰብ ክፍል ማለትም ህፃናት፣ታዳጊዎች፣አዋቂዎች፣የልዩ ፍያለባቸላጎት ያለቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ማለት ነው፡፡

**አንቀጽ 9፡ የማህበሩ መቀመጫ**

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሰርከስ ጥምረት ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 10፡ የማህበሩ የአባላት አይነት**

10.1 መስራች አባላት

10.2 የክብር አባለት

10.3 ተባባሪ አባለላት ይኖሩቷል፡፡

<u>የማህበሩ መስራች አባላት</u>

1. በሃገር አቀፍ የሲቪል ማህበራት ኤጀንሲ ወይም በክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የእውቀና ሠርተፍኬት በተሰጠው የሰርከስ ማህበር የተወከለ ወይም በክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የድጋፍ ደብዳቤ የሚያቀርብ 2(ሁለት) አባላት ለግዜው የሚያሳትፍ ሲሆን በቀጣይ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወሰነው መሰረት ቁጥሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡
2. መስራች አባላት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተገዢዎችና በስራቸው ለሚገኙት አባላቶች (ቡድኖች) ሙሉ ሃላፊነት መወሰድ አለባቸው፡፡
3. በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰነውን መዋጮና ክፍያዎችን በተመለከተ በየማህበራቸው ስም መክፈል አለባቸው፡፡

<u>የማህበሩ የክብር አባላት</u>

1. ዘርፉ አሁን ላለበት ደረጃ እንዲደርስ በግልም በተቃምም ከፍተኛ አስተዋፅዎ ያደረገ ግለሰብ ወይንም ማህበር
2. ዘርን ለማሳደግ በቀጣይ ትልቅ አስተዋፅዎ ያደርጋል ተብሎ ታስቦ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ግለሰብ ወይንም ተቋም
3. በጥምረቱ በስራ አስፈፃሚነት ለረጅም ግዜ በማገልገል በጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ግልሰብ የክብር አባል ይሆናል፡፡

<u>የማህበሩ ተባባሪረ አባል</u>

1. በዘርፉ ተባባሪ ሆኖ ሲሰራ የቆየ ግለሰብ ፣ቡድን ወይንም ተቋም

2. በቀጣይ የዘርፉ እድገት ላይ በትብብር በመሰራት አስተዋፅዎ ያደርጋል ተብሎ የታሰበ ግለሰብ፣ቡድን ወንም ተቃም በጠቅላላ ጉባዬ ቀርቦ በአብላጫ ድምፅ ተቀባይነት ያገኘ ግልሰብ የክብር አባል ይሆናል፡፡

### 10.1 አዲስ ጥምረቱን ለመቀላቀል ለሚፈልጉ አባላት መመዘኛ ለመስፈርት

የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ በጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ ተቀባነት ያገኙ የአገራችንን የክልል ሰርከስ ማህበር የማህበሩ አባል መሆን ይችላል፡፡

1. የማህበሩን ህግንና ደንብ የሚያከብር፣
2. በአገራችን ክልሎች ውስጥ ኖሮ በስሩ ህጋዊ የሆኑ ሰርከሶችን የያዘ/ከተማ አስተዳዳር ከሆነ ብቻውንም ቢሆን ይወከላል
3. በክልል ደረጃ ህጋዊ የክልል ሰርተፍኬት የሚያቀርብ/ከክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የውክልና ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል
4. በማህበራት አደረጃጀት መሰረት የማህበሩን የስራና የሂሳብ ሪፖርት በወቅቱ ማቅረብ የሚችል
5. በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፈል የሚችል፣
6. የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚወጡ የስነምግባር ደንቦችን በማህበራቸው ተግባራዊ የሚያደርግ፣

### አንቀጽ 11፡ የአባላት መብት

ሁሉም በማህበሩ ስር የተመዘገቡ ሰርከሶች እኩል መብት አላቸው፣ ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል፡-

ሀ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውም መረጃ/ሪፖርት ጠይቆ

የማግኘት፣

ለ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት

መብት አለው፡፡

ሐ. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ

በፊት በስራ አስፈጻሚው የመሰማት መብት አለው፡፡

መ. ማንኛውም አባል ከማህበሩ በሚሰናበት ጊዜ በማህበሩ ውስጥ በነበረው እንቅስቃሴ የሚያሳይ የመልቀቂያ ደብዳቤ/ሰርተፍኬት የማግኘት መብት አለው፡፡

### አንቀጽ 12፡ የአባላት ግዴታ

1. ለማህበሩ ዓላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፣
2. ማንኛውም አባል የአባልነት መዋጮውን በወቅቱ መክፈል አለበት
3. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ/ቷ በፊት የሚፈለግበትን/ የሚፈለግባትን ዕዳ መክፈል ይኖርታል
4. ማንኛውም አባል የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችና ውሳኔዎችን ማክበር አለበት
5. ማንኛውም አባል የማህበሩን ዓላማና የገባቸውን/የገባቸባቸውን ግዴታዎች ማክበር፣የማህበሩን ንብረት የመንከባከብና የመጠበቅ ግዴታ አለበት
6. በማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት

### አንቀጽ 13፡ የንዑስ አባላት መብት እና ግዴታ

ማህበሩ እደ አስፈላጊነቱ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰየሙ ንዑስ ኮሚቴ ይኖሩታል፡፡ ሁሉም ንዑስ አባላት እኩል መብት አላቸው፣ ማንኛውም የማህበሩ ንዑስ አባል፡-

ሀ. ስለማህበሩ ዓላማና ተልዕኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፣

ለ. ስለማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ/ ሪፖርት ከቡድኑ መሪዎች ጠይቆ የማግኘት፣

ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ ላይ በማህበርና ቡድን መሪዎች ውክልና የመገኘት፣ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት መብት አለው፡፡

መ. ማንኛውም የማህበሩ ንዑስ አባል አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት

በቡድኑ መሪና በማህበራ፣በበድን መሪና በማበሩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የመሰማት መብት አለው፡፡

ሠ. ማንኛውንም አባል የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ

መመሪያዎችና ውሳኔዎችን ማክብር አለበት፣

ረ. ማንኛውም አባል የማህበሩን ዓላማና የገባቸውን ግዴታዎች ማክበር፣

የማህበሩንንብረት የመንከባከብና የመጠበቅ ግዴታ አለበት፣

**አንቀጽ14. በተመዘገቡ ማህበራና አባላት የአርቲስቶችና የተማሪዎችን ዝውውር በተመለከተ**

- በዚህ ደንብ  አንቀጽ 11 የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሰርከስ ጥምረት የውስጥ ደንብ መሰረት እኩል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ15. የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች**

1. የማህበሩ መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የሚደረጉበት ጊዜና መጠን በጠቅላላ ጉባዔው ይወሰናል፡፡
2. በጠቅላላ ጉባኤው በሚወሰነው የጊዜ ገደብ የማይከፍል በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መቀጮ ይጣልበታል፡፡
3. የአባልነት መዋጮ ባለመከፈሉ ምክንያት በጠቅላላ ጉባኤው የተጣለበትን/የተጣለባትን ቅጣት ያልከፈለ አባል ላይ እዳውን እስኪከፍል ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው ድምጽ የመስጠት ወይም ማንኛውንም ሌላ ለሙብት ሊያነሳ ይችላል፡፡


**አንቀጽ 16፡ አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች**

አንድ የማህበሩ አባል አባልነቱ የሚቋረጠው፤

1. ማህበሩ ሲፈርስ
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሰረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣
3. የማህበሩን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፍ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
4. ለማህበሩ ዓላማ መሳካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሳትፎ ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን ሲቀር እና ይኸውም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
5. መዋጮውን ለአንድ አመት ያህል ጊዜ ባለመክፈሉ በጠቅላላ ጉባኤው ከአባልነቱ ሲሰናበት
6. ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት መብቱን ሲነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ
7. ከማህበሩ አባልነት በራሱ ፍቃድ ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ ይሆናል፣

**አንቀጽ 17፡ የማህበሩ አደረጃጀት**

1. ማህበሩ  የሚከተሉት የአደረጃጀት መዋቅር ይኖሩታል፡፡
   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ
   ለ. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
   ሐ. የውስጥ ኦዲተር
   መ. ንኡሳን ኮሚቴ እና ሌሎች ሠራተኞች ይኖራሉ፡፡
2. ማህበሩ በሚከተው መልኩ የተዋቀረ ነው፡-




3. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ሆኖ ሊሰራ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 18፡ የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ስልጣንና ተግባር**

የጠቅላላ ጉባኤው ኣባላትና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ኣባላት የሚመረጡት በሃገሪቱ ካሉ በየክልሉና ልዩ የከተማ መስተዳድሮች ከሚገኙ ሃገራዊ የጥምረቱ ኣባል የሰርከስ ማህበራት የሆኑ በሰርከስ ጥበብ ባገር ውስጥና በውጭ ኣገር የረጂም ግዜ የሙያ ልምድ ያላቸው በተልይም በሰርከስ ዳይሬክተርነት፤ በኣሰልጣኝነት፤ በኣዘጋጅነት፤ በኣስተዳዳሪነት፤ በዳኝነት ወይም ተያያዥ ስራዎች የረጅም ግዜ ልምድ ባላቸው ባለሞያዎች የሚዋቀርና ዝርዝር መስፈርቱ በውስጣዊ መመርያ መሰረት የሚወሰን ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸው እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተጠቀሱትን አባላት የሚያካትት ሆኖ በህግና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-
   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይ አካል ነው፡፡
   ለ. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣
   ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የማህበሩን ኦዲተር ይመራል፣ ያሰናብታል፣ ክፍያውን ይወስናል፣
   መ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን፣ የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሐፊ ይሾማል፡፡ ይሽራል፣
   ሠ. የማህበሩን ዋና መስሪያ ቤት የመለወጥና ቅርጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ውሳኔ ያሳልፋል፣
   ረ. የማህበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያጸድቃል፡፡
   ሰ. ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣
   ሸ. በማህበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣
   ቀ. በማህበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
   በ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9 በተገለጸው መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣

ተ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣
ቸ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣
ነ. ማህበሩ ከሌሎች ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሠጣል፣
ኘ. በማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፡፡

2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ረ)፣ (ቸ) እና (ኀ) መሰረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማህበሩ አካላት ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል፡፡
3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናል፡፡
5. የጠቅላላ ገጉባዔ ምልዓተ ጉባዬ 50 + 1 ሲሆን የተማላ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 19 የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥ

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ድምጽ በሚሰጥበት ጉዳት ላይ የሚሰጠው ድምጽ በማህበሩ ሲወከሉ ሁለት ድምፅ በግል ሲሆን አንድ ብቻ ይሆናል፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ እራሱ ተገኝቶ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል፡፡
3. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሥርዓት ፍትሀዊ ነጻና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. ከጠቅላላቀው ጉባኤ የተለየ ሃሳብ ያለው የማህበር አባል የልዩነት ሀሳቡን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል፡፡
5. ማንኛውም መደበኛ የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሳኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ይጥሳል ብሎ ሲያምን/ስታምን ለኢጀንሲው ሊያመለክት ይችላል/ትችላለች፡፡
6. የክብር አባላትና ተባባሪ አባላት በጠቅላላ ጉባዔ ላይ ያለድምጽ ይሳተፋሉ ፡፡

## አንቀጽ 20፡ የጠቅላላ ጉባኤው አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውምየሚከተለው ነው፣

1. **የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሰቢ፣**

   ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል ከጻሀፊው ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል

   ለ. የጉባኤውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል

   ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል

   መ. ጉባኤው ያጸደቃቸው ዓመታዊ የሥራ ክንውን፤ የሥራና የኦዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል

   ሠ. ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለጸሐፊው በአጀንዳነት ያስይዛል፣

### 2. ምክትል ሰብሳቢ

ሀ. ሰብሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተከትሎ/ታ ይሠራል/ትሰራለች፣

ለ. በሰብሳቢው/ዋ ወይም፣ በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል/ታከናውናለች፣

### 3. ጸሐፊ

ሀ. ከሰብሳቢው/ዋ ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

## አንቀጽ 21፡ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንብር ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ 30 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል፡፡
2. የማህሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በፐሬዝዳንቱ ወይም በሊቀመንበሩ/ሰብሳቢ ከማህበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፤
3. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ ቀኑን፤ ጊዜውን እንዲያውቁት ይደረሃል፡፡
4. የማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሆናል፡፡
5. ከላይ በአንቀጽ18 በንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡
6. በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዩች እንደየ ሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳ እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ፀሐፊ/ፐሬዝዳንቱ/ የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ/ በጽሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡

## አንቀጽ 22፡ የምርጫና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ማህበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣
2. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፣
3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣
4. ጠቅላላ ጉባኤው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሸሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓዳሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ለመተካት እንደ አስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣
5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቁ ተመራጮች በድጋሜ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ አንድ የምርጫ ዘመን /4 ዓመት/ መቆየት ይኖርባቸዋል፡፡
6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
7. የማህበሩ የስብሰባ ስነ-ስርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተከተለ መሆን አለበት
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በእጩነት ማቅረብ አይችሉም ሆኖም የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፡፡
9. የአስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እራሳቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት
10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱበት እለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ውጭ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፡፡
11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳነት ቀርበው ያልጸደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሳኔዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**አንቀጽ 23. የስራ አስፈጻሚ አባላት ዝርዝር**

| | ስም | ሃላፊነት |
|---|---|---|
| 1. | | ፕሬዝዳንት |
| 2. | | ም/ፕሬዚዳንት |
| 3. | | ጸሃፊ |
| 4. | | ሂሳብ ሹም |
| 5. | | ገንዘብ ያዥ |
| 6. | | አባል |
| 7. | | አባል |

**አንቀጽ 24. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባራት**

1. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለጠቅላላ ጉባኤው የሚቋቋምና ተጠሪነቱን ለዚሁ አካል ሆኖ የእለት እለት ስራ ያከናውናል፡፡
2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባራት ይኖሩበታል፡፡

ሀ የማህበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት በጀት ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

ለ. የማህበሩን ዓመታዊ የስራ መርህ ግብርና አጭር የመካከለኛና ረጅም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

ሐ. የማህበሩን አላማዎች ለማስፈጸም ገቢ ምንጮችን የገንዘብ፣ የጉልበት/ የማቴሪያል ድጋፍ የሚገኝበተርን ዘዴ ያፈላልጋል፡፡

መ. የማህበሩን ፖሊሲ በማመንጨት ያቀርባል፡፡

ሠ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎች በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

ረ. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያስወስናል፡፡

ሰ. አባልነት ግዴታቸውን ያልተወጡ አባላት እንዲሰርዙ ለጠቅላላ ጉባኤው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

ሸ. የራሱ ያሰራር ስነ-ስርዓት ያወጣል፡፡

ቀ. በጠቅላላ ጉባኤው የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

በ. የማህበሩን መደበኛ አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፡፡

**አንቀጽ 25 የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት**

1. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡
   ሀ. ፕሬዝዳንት
   ለ. ም/ፕሬዝዳንት
   ሐ.ፀሐፊ
   መ. ሒ/ሹም
   ሠ. ገ/ያዥ
2. ፕሬዝዳንቱ/ፕሬዝዳንቷ

በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን የሚከተሉትን ስራዎችን ያከናውናል፡፡

ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚቋቁማቸውን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎችን በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡

ለ. የማህበሩን በ3ኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡

ሐ. በማህበሩ ስም የተከፈተውን የባንክ ሒሳብ ቼኮችንና የወጭ ሰነዶችን የሒሳብ ሹሙ ጋር በመሆን በጣምራ ይፈርማል፡፡

መ. ለማህበሩ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ይፈቅዳል፡፡

ሠ. የ3 ወር፣ የ6 ወር እና ዓመታዊ የሥራ እና የፋይናንስ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

ረ. በማህበሩ ሥራ ደብዳቤዎችን ይፈርማል፡፡

ሰ. ሂሳብ ሹምና ገነዘብ ያዡን ጨምሮ በሥራ የሚገኙትን ሠራተኞች እያስተበበረ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የማህበሩን የዕለት ተእለት ሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡

ሸ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በማስፈቀድ በማህበሩ ሥራ ንብረት ለመግዛትና ለመሸጥ ሚያስችሉ ውሎችን ይዋዋላል፡፡

ቀ. በጠቅላላው ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በተግባር ላይ ያወላሉ፡፡

በ. ሌሎች ለሥራ አስፈጻሚው የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል፡፡

ተ. ማህበሩ በሚከሰስበትም ሆነ በሚከሰበት ወቅት ጠበቃ በመወከል ጉዳዩን ይከታተላል፡፡

**3. ምክትል ፕሬዝዳንቱ/ቷ፣**

ሀ. ፕሬዝዳንቱ/ቷ በማይኖሩበት ጊዜ ፕሬዝዳንቱን/ቷን ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሰራል/ትሰራለች፡፡
ለ. ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የማህበሩን የመጻጻፍ ግንኙነት ሥራዎች ያከናውናል፡፡

**4. ፀሐፊው/ዋ**

ሀ. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡
ለ. ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የማህበሩን የመጻጻፍ ግንኙነት ሥራዎች ያከናውናል፡፡
ሐ. የስራ አስፈጻሚውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡፡
መ. የማህበሩን ማህተም፣ ሰነድና መዛግብት ይይዛል፡፡
ሠ. የአባልነት ማመልከቻዎችን ይቀበላል፡፡

**5. ሒሳብ ሹም**

ሀ. የማህበሩን ገቢና ወጪ ሂሳብ በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡

ለ. የማህበሩ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሳብ አሠራር ደንብ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሐ. በማህበሩ ሥም የተከፈተውን የባንክ ሒሳብ ቼክና የወጪ ሰነዶች ላይ ከፕሬዝዳንቱ ጋር ወይም ከምክትል ፕሬዝዳንቱ ጋር በጣምራ ይፈርማል፡፡

መ. የማህበሩ የሂሳብ መዛግብት በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

ሠ. የሂሳብ መዝገቡ፣ ገቢና ወጭ፣ ኃብትና እዳን ያከተተ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

ረ. ማህበሩ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ በሚሰማራበት ጊዜ ለዚሁ ሥራ ሚውሉ የተለያዩ የሂሳብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

6. የማህበሩ ገንዘብ ያዥ፣

ሀ. የማህበሩን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፡፡

ለ. የተሰበሰበውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣

ሐ. ለሥራ ማስኬጃና ለማህበሩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 10,000.00 (ሶስት ሽህ ብር) ያልበለጠ ገንዘብ ይይዛል፡፡

መ. ከሒሳብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሒሳብ በየወሩ ያመሳክራል፡፡

ሠ. የማህበሩን ቼክ ይይዛል፡፡

ረ. በጣምራ ፊርማ በሒሳብ ሹሙና በፕሬዝዳንቱ በወጪ ሰነድ ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 26፡- የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስብሰባ፣ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት**

**የአባላት የአገልግሎት ዘመን**

1. የኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በዓመት ስድስት ጊዜ የሚከናወን ሲሆን አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲሆን ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዝዳንቱ ወይም በ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ውክልና ሊጠራ ይችላል፣
3. ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓት ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በድጋሜ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምጽ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ፕሬዝዳንቱ የደገፈው ሃሳብ ይጸናል፣
5. የኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አንድ የኮሚቴ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፣

**አንቀጽ 27፡ የኦዲተር ኃላፊነት ተግባር**

1. የማህበሩ ኦዲተር የማህበሩ ፕሬዝዳንት ወይም የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሊሆን አይችልም፡፡
2. ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላው ጉባኤው ጉባኤው ሆኖ፤ የሚከተሉት ሥልጣን ተግባሮች ይኖሩታል፤

2.1. የማህበሩን የገንዘብ የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣

2.2. የማህበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣

2.3. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሰረት ዓመታዊ የኦዲተር ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፤

**አንቀጽ 28፡ የማህበሩ የገቢ ምንጭ**

የማህበሩ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከሕዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 29፡ ስለማህበሩ መዋሃድና መለወጥ**

1. ማህበሩ ወደተለያዩ ማህበራት የሚከፋፈለው፣ ከሌላ ማህበር ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ በጎ አድራጎት ድርጅትነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ ¾ኛ ድምጽ ሲወስን ነው፡፡
2. ከማህበሩ ጋር የሚዋደደው ማህበር ጋር የሚደረገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ጸሀፊና የማህበሩን ፕሬዝዳንት ማካተት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 30፡ ስለማህበሩ መፍረስ**

1. ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ ¾ኛ ድምጽ ሲወሰኑ ነው፡፡
2. ማህበሩ በሚፈርስበት ሰዓት ተመዝግበው በሚገኙት አባላት እንደየ አገባበቸው የንብረት ክፍፍል ያደርጋሉ
3. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩ ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ሁለት ወራት ሳያልፍ የማህበሩ ፕሬዝዳንት የንብረት ቆጠራ /inventory/ ሰርቶ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለማህበሩ አባላት እንደየ ድርሻቸው ክፍፍል ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 31፡ የመተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ የመተዳደርያ ደንብ ከመስከረም 19 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 32፡ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል**

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ¼ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል፡፡
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ጸሀፊ ወይም ፕሬዝዳንት ጉባኤው ጥሪ ከመስራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሀሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ¾ኛ ድምጽ ሲያገኝ ነው፡፡

የመስራች አባልት ስምና ፊርማ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| 8 | | |
| 9 | | |
| 10 | | |
| 11 | | |
| 12 | | |
| 13 | | |
| 14 | | |